# كيفية صلاة النبي صلى اللّه عليه وسلم

## سماحة الشيخ عبد اللّه بن عبد العزيز بن باز رحمه الله

قام بترجمته إلى الأمهرية

## الأستاذ محمد فرج مغنو

# የነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም የሰላት አሰጋገድ

## ሸይኽ አብዱል አዚዝ ብኑ ባዝ

ወደ አማርኛ ተርጓሚ

## ኡስታዝ ሙሐመድ ፈረጅ መገኖ

طبع على نفقة وصية خولة دخيل الجسار رحمها الله (دولة الكويت) بإشراف اتحاد علماء إفريقيا

የህትመት ወጪው የተሸፈነው በኸውላ ደኺል አልጂሳር አላህ ይዘንላት ኑዛዜ አስፈጻሚ ( ከኩወይት ሀገር) በአፍሪካ ኡለማዎች አንድነት የበላይ ተቆጣጣሪነት

1437/2016

<u>እጅግ አዛኝና ሩህሩህ በሆነው አላህ ስም</u>

# የነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም የሰላት አሰጋገድ[1]

ምስጋና ሁሉ ለአላህ ብቻ ይሁን የአላህ ውዳሴና ሰላም በነብያችን ሙህመድ ላይ እንዲሁም በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን ፡፡

ከዚህ በማስከተል ፡-

ይህቺ የነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም የሰላት አሰጋገድን በተመለከተ አጭር መልዕክት ነች ፡

ይህን ለማዘጋጀት ያነሳሳኝ ሁሉም ሙስሊም ወንድም ሆነ ሴት እቺን መጽሀፍ አንብቦ የነብዩን ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም አይነት ሰላት ለመስገድ እንዲተጋ በማሰብ ነው ፡ነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋልና ፡(( እኔ ስሰግድ እንዳያቻሁኝ ስገዱ )) ቡኻሪ ዘግበውታል [2]፡፡ በዚህ መነሻ ለአንባቢያን እንደሚከተለው ቀርቦዋል ፡፡

1- ወዱእን ያዳርስ እሱም ፡- አላህ እንዲህ ብሎ ባዘዘው መሰረት ወዱእ ያድርግ ፡(እናንተ ያመናችሁ ወደ ሶላት በቆማችሁ - ለመቆመ ባሰባችሁ - ጊዜ ፊቶቻችሁን፤ እጆቻችሁንም እስከ ክርኖች እጠቡ ፡፡ ራሶቻችሁንም - በውሃ - እበሱ ፡፡ እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች - እጠቡ- )) አንቀጹ ይቀጥላል[3] ፡፡

- የአላህም መልእክተኛ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል (ያለ መጸዳዳት የሚሰገድ ሰላት ተቀባይነት የለውም )[4] እንዲሁም ፡ ለዛ ሰላቱን ላበላሸው ሰው የሰጡት ምክር ላይ እንዲህ ብለዋል ፡- ( ለሰላት መቆም ስታስብ ወዱእን አዳርሰህ አድርግ …. )[5]

2- ሙስሊም ሲሰግድ ቂብላን ይቅጣጫል ፡ እሱም ፡- ወደ ከዕባ ነው ፡ የትም ቢሆን የሚሰግደውን ሰላት ሱናም ይሁን ዋጅብ በልቡ እያሰበ በሙሉ አካሉ ወደ ከዕባ ይቅጣጫል ፡፡ ለመስገድ ያሰበውን ሰላት በምላሱ አይናገር ፡ በምላስ መናገሩ አልተደነገገምና ፡ ይልቁንም አዲስ ነገር ነው ፡ ነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲሁም ባልደረቦቻቸው ስላላደረጉት ፡፡ ለብቻው ወይም መሪ ሆኖ ሲሰግድ ከፊት ለፊቱ ከለላ ያድርግ ፡፡ ወደ ቂብላ መዞር ለሰላት መስፈርት ነው ፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች በስተቀር እሱም በእውቀት ባልተቤቶች (የፊቅሂ) መጽሀፍት በግልጽ ተብራርቶዋል ፡፡

3- የሰላት መከፈቻውን ተክቢራ እንዲህ በማለት ይጀምራል ፡ ወደ ሱጁድ መውረጃ ቦታ እያየ اللهُ أَكْبَرُ አላሁ አክበር ይላል - አላህ ኩሉም ይበልጣል- ፡፡

4- አላሁ አክበር ሲል እጆቹን ወደ ተከሻው ወይም ወደ ጆሮው አቅጣጫ ከፍ ያደርቸዋል ፡፡

5- ቀኝ እጁን በግራው መዳፍ ጀርባ ላይ በማድረግ እጆቹን ደረቱ ላይ ያሰቀምጥ ፡ በዚህ መልኩ ከነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ስለተገኘ ፡፡

---

[1] ከኩቡርነታቸው ቤተ መጽሀፍት ተገኝታ በመጣጥፍ መልኩ የተሰራጨች መልዕክት ናት

[2] (አልቡኻሪ አልአዛን (605) ፤ አዳሪሚ ዘሰላት (1253)

[3] ሱረቱ አልማኢዳህ 6 አንቀጽ

[4] ሙስሊም አጠሃረህ (224) ፤ አቱርሙዚይ አጠሃረህ (1) ፤ ኢብኑ ማጀህ አጠሃረህ ወሱነኑሃ (272) ፤ አህመድ (2/73)

[5] አልቡኻሪ አል ኢስቲእዛን (5782)  አል አይማን ወኑዞር (6174) ፤ ኢብኑ ማጀህ ኢቃመቱ አሰላት ወአሱነቱ ፊሃ (441)

6- የመክፈቻ ዱዓ ማድረግ ይወደዳል እሱም :- (اَللَّهُمَّ بَاعِدْ بَيْنِي وَبَيْنَ خَطَايَايَ كَمَا بَاعَدْتَ بَيْنَ اَلْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ , اَللَّهُمَّ نقِّنِي مِنْ خَطَايَايَ كَمَا يُنَقَّى اَلثَّوْبُ اَلْأَبْيَضُ مِنْ اَلدَّنَسِ , اَللَّهُمَّ اِغْسِلْنِي مِنْ خَطَايَايَ بِالْمَاءِ وَالثَّلْجِ وَالْبَرَدِ)

*(አላሁመ ባኢድ በይኒ ወበይነ ኸጣያየ ከማ ባአድተ በይነል መሽሪቂ ወል መግሪቢ ፤ አላሁመ ነቂኒ ሚን ኸጣያየ ከማ ዩነቃ አሰውቡ አል አብየዱ ሚነ ኣደነስ ፤ አላሁመ ኢግሲልኒ ሚን ኸጣያየ ቢልማኢ ወሰልጂ ወልበረድ)* ፡፡ ከፈለገ በዚህ ፋንታ ይህንም ማለት ይችላል :- (سُبْحَانَكَ اَللَّهُمَّ وَبِحَمْدِكَ تَبَارَكَ اِسْمُكَ , وَتَعَالَى جَدُّكَ , وَلَا إِلَهُ غَيْرُكَ)

*(ሱብሃነከ አላሁመ ወቢሀምዲከ ወተባረከ ኢስሙከ ወተዓላ ጀዱከ ወላ ኢላሀ ገይሩከ)* ፡ ቱርጉሙ ፡ ጌታዬ ሆይ ምስራቅንና ምዕራብን እንዳራራክ በእኔና በወንጀሌ መሀል እንደዚህ አራርቅ ፡ ጌታዬ ሆይ ነጭ ልብስ ከእድፉ እንደሚጸዳ እኔንም ከወንጀሌ እንደዚሁ አጽዳኝ ፤ ጌታዬ ሆይ ከወንጀሌ በውሃ፤ በበረዶ እና በጤዛ እጠበኝ ፡፡

ጌታዬ ሆይ ከምስጋናህ ጋር ጥራት ይገባህ ፡ስምህ የተባረከ ነው ፡ልቅናህ ከፍ ያለ ነው ፡ ካንተ በስተቀር የሚመለክ የለም [1] ፡፡ በዚህ ቦታ ከነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም የተገኙትን ከእነዚ ሌላ ዱአዎችን ቢተገብር ችግር የለውም ፡ ሁሉንም በተለያየ ግዜ መጠቀሙ በላጭ ነው ፡ ነብዩን ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ሙሉ በሙሉ መከተል ስለሚያስገኝ ፡፡ ከዚያን እንዲህ በማለት በአላህ ከሸይጣን ይጠበቅ *(አኡዙ ቢላሂ ሚነ አሸይጣኒ አረጂም ፡ ቢስላሂ አረህማኒ አረሂም )*

{أَعُوذُ بِاَللَّهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ ، بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَنِ الرَّحِيمِ}

ከዚያን የፋቲሃን ምዕራፍ ያንብብ የአላህ መልዕክተኛ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ እንዲህ ብለዋልና ፡ (- ሰላት ውስጥ- የፋቲሃን ምዕራፍ ያላነበበ ሰላት የለውም )[2] ፋቲሃን አንደጨረሰ ፡ ድምጽ ከፍ በሚደረግባቸው ሰላቶች ድምጹን ከፍ አድርጎ ዝቅ በሚደረግባቸው ዝቅ አድርጎ - አሚን - ይላል ፡፡ ከዚያን የገራለትን የቁርዓን አንቀጾች ያንብብ ፡ በላጩ በዙህር ፤ በአስር እና በኢሻ ሰላቶች ከተከፋፈሉት ውስጥ መካከለኛ ምዕራፎችን[3] ፡ ማንበብ ነው ፡ በሱብሂ ሰላት ከተከፋፈሉት ውስጥ ረጃጅሞችን ማንበብ፡ በመግሪብ ሰላት ከተከፋፈሉት ውስጥ አንዳንዴ አጫጭሮችን አንዳንዴ ረጃጅሞችን ማንበብ፡ በዚህ ዙርያ የተዘገቡ ሀዲሶችን ለመተግበር ሲባል ፡፡

7- እጆቹን ወደ ትከሻው ወይም ወደ ጆሮዎቹ አቅጣጫ እያነሰ አላሁ አክበር ብሎ ያጎንብስ ፡ ጭንቅላቱን ከወገቡ ትይዩ ያድርግ የእጆቹን ጣቶች በመነጣጠል ጉልበቱ ላይ ያደርግ በዚህ ሁኔታ

[1] አልቡኻሪ አል አዛን (711) ፤ ሙስሊም አልመሳጅድ ወመዋኢድ አሰላት (598) ፤ አነሳኢይ አል ኢፍቲታህ (895) ፤ አቡ ዳዉድ አሰላት (781) ኢብኑ ማጀህ ኢቃመቱ አሰላት ወአሱነቱ ፊሃ (805) ፤ አህመድ (2/231) ፤ አዳረሚይ አሰላት (1244)

[2] አልቡኻሪ አልአዛን (723) ፤ኢብኑ ማጀህ ኢቃመቱ አሰላት ወ አሱነቱ ፊሃ (837) ፤አህመድ (5/316) ፤ አዳረሚይ አሰላት (1242) ፤ አነሳኢይ አል ኢፍቲታህ (911) ፤ አቡ ዳዉድ አሰላት (822) ፤ አቱርሙዚይ አሰላት (247)

[3] የተከፋፈሉ የሚባሉት ከሱረቱ ቃፍ እስከ ሱረቱ አናስ ያሉ ምዕራፎች ሲሆኑ ፡ከ ቃፍ እስከ አማ ያሉት ረጃጅም ይባላሉ ፡ ከአማ እስከ አዱሃ ያሉት መካከለኛ ይባላሉ ፡ ከአዱሃ እስከ መጨረሻው ያሉት አጫጭር ይባላሉ ፡፡ ( ይህ ነጥብ ከቶርጋሚው ነው )

ሳለ እንዲህ ይበል *:(ሱብሃነ ረቢየል አዚም* سُبْحَانَ رَبِّيَ الْعَظِيمِ) ሀያሉ ጌታዬ ጥራት ይገባህ :ይህን ሶስቴ ወይም ከዚያ በላይ መደጋገሙ ይመረጣል :በተጨማሪ እንዲህ ቢል ይወደዳል :- *(ሱብሃነከ አላሁመ ወቢሀምዲከ ፡ አላሁመ ኢግፊር ሊ )* ፡፡ ( سُبْحَانَك اللهم وبِحَمدِك ، اللهم اغْفِر لي) [1] (ጌታዬ ከምስጋናህ ጋር ጥራት ይገባህ ያ አላህ ማረኝ ) ፡፡

[1] አልቡኻሪ ተፍሲሩል ቁርዓን (4683) ፤ ሙስሊም አሰላት (484) ፤ አነሰኢ አተጥቢቅ (1122) ፤ አቡ ዳውድ አሰላት (877) ፤

8- እጆቹን ወደ ትከሻው ወይም ጆሮው አቅጣጫ እያነሳ ካነሰበት እንዲህ እይለ ቀና ይበል ፡ ብቻውን ሚሰግድ ወይም ኢማም (መሪ) ሁኖ ሚያሰግድ ከሆነ *(ሰሚ አላሁ ሊመን ሀሚደህ* ፡ ይበል سَمِعَ اللَّهُ لِمَنْ حَمِدَهُ )[1] ከዚያን ቆሞ እያለ እንዲህ ይበል *(ረበና ወለከ አል ሀምዱ ሀምደን ከሲረን ጠይበን ሙባረከን ፊሂ ሚልአ አሰማዋቲ ወሚልአ አልአርዲ ወሚልአ ማሺእተ ሚን ሸይኢን በእዱ* ) ( رَبَّنَا وَلَكَ الْحَمْدُ حَمْدًا كَثِيرًا طَيِّبًا مُبَارَكًا فِيهِ مِلْءَ السَّمَاوَاتِ ، وَمِلْءَ الأَرْضِ ، وَمِلْءَ مَا شِئْتَ مِنْ شَيْءٍ بَعْدُ)[2] ጌታችን ሆይ ያማረ፤የበዛ፤የተባረከ፡ሰማይን፤ ምድርን ፤በሁለቱ መሀል ያለንም፤ ከዚህም በላይ አንተ ያሻህውን ቦታ ሁሉ ፡ የሞላ ምስጋና ላንተ ይድረስህ ፡፡ ተከታይ (መእሙም) ሁኖ ሚሰግድ ከሆነ ቀና ሲል ቅድም ያለፈውን እስከ መጨረሻው ይበል ፡ እሱም ፡(ረበና ወለከ አልሀምዱ ... )፡ ሁሉም ማለትም መሪ ተከታይ ( ኢማሙም ፡ መእሙሙም) እና ለብቻው ሚሰግደውም በተጨማሪ ይህን ቢሉ ጥሩ ነው ከነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ስለተገኘ ( أَهْلَ الثَّنَاءِ وَالْمَجْدِ , أَحَقُّ مَا قَالَ الْعَبْدُ –وَكُلُّنَا لَكَ عَبْدٌ– اَللَّهُمَّ لَا مَانِعَ لِمَا أَعْطَيْتَ , وَلَا مُعْطِيَ لِمَا مَنَعْتَ , وَلَا يَنْفَعُ ذَا اَلْجَدِّ مِنْكَ اَلْجَدُّ )[3]

[1] አልቡኻሪ አል አዛን (657) ፤ ሙስሊም አሰላት (411) አቡ ዳውድ አሰላት (601) ፤ ኢብኑ ማጀህ ኢቃሙቱ አሰላት ወ አሱነቱ ፊሃ (1238) ፤ አቱርሙዚይ አሰላት (361) ፤ አነሰኢይ አል ኢማመህ ( 832) ፤ ማሊክ አኒዳእ ሊ አሰላት (306) ፤ አዳረሚይ አሰላት (1256)

[2] ሙስሊም ሰላቱ አል ሙሳፊሪና ወቀስሩሃ (771) አቡ ዳውድ አሰላት (760) ፤ አቱርሙዚይ አደዐዋት (3423) ፤ አህመድ (1/103)

[3] ሙስሊም አሰላት (477) አቡ ዳውድ አሰላት (847) ፤ አነሰኢይ አተጥቢቅ ( 1068) ፤ አህመድ (3/87) ፤ አዳረሚይ አሰላት (1313)

(አህሉ አሰናእ ወልመጅድ አሀቁ ማቃለ አል አብዱ ወኩሉና ለከ አብዱን አለሁመ ላ ማኒአ ሊማ አእጠይተ ወላ ሙእጢየ ሊማ መነእተ ወላ የንፈኡ ዛ አልጀዲ ሚንከ አልጀዱ ) ፡ የልቅና የመወደስ ባለቤት የሆንከው ጌታችን ፡ባርያው ካለው የበለጠ ነው ሚገባህ ፡ ሁላችንም ላንተ ባርያ ነን ፡ ጌታዬ ሆይ አንተ ለሰጠህው ከልካይ የለውም ፡ አንተ ለከለከልከው ሰጪ የለወም ፡ ባለ ሀብት ሀብቱ አያብቃቃውም ፡ ሚያብቃቃው አንተን መታዘዝ ብቻ ነው ፡፡ በዚህ ቦታ ፡ ከሩኩእ /ከማጎንበስ/ በፊት እንደነበረው ፡ለሁላቸውም እጃቸውን ደረታቸው ላይ መኖር ይወደዳል ፡ ይህን የሚያመላክት መልእክት ዋኢል ብኑ ሀጀር እና ሰህል ብን ሰእድ አላህ ይዘንላቸውና ከነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም በዘገቡት ስለተገኘ ፡፡

9- አላሁ አክበር እያለ ሱጁድ ይውረድ ፡ ከቻለ ከእጆቹ በፊት ጉልበቶቹን መሬት ያኑር ፡ ይህ አወራረድ ካስቸገረው እጆቹን ከጉልበቶቹ ያስቀድም ፡ በእጆቹና በእግሮቹ ጣቶች ወደ ቅብላ ይቅጣጭ ፡ የእጆቹን ጣቶች ሰብሰብ ያድርግ ፡፡ በሰባት አካሎቹ መሬት ይንካ ፡ እነሱም ፡ ግንባር ከአፍንጫ ጋር ፤ የሁለት እጆች መዳፋቸው ፤ ሁለት ጉልበቶች እና የሁለት እግሮች የጣቶቻቸው ውስጡ ናቸው ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሳለ እንዲህ ይላል ፡( سُبْحَانَ رَبِّيَ الأَعْلَى ሱብሃነ ረቢየል አእላ)ከፍ ያለው ጌታዬ ጥራት ይገባው፡ ከዚህ በተጨማሪ እንዲህ ማለት ይወደዳል፡[1] ( سُبْحَانَكَ اَللَّهُمَّ رَبَّنَا وَبِحَمْدِكَ اَللَّهُمَّ اِغْفِرْ لِي (ሱብሃነከ አላሁመ ረበና ወቢሀምዲከ አላሁመ ኢግፊር ሊ) ጌታችን ሆይ ከምስጋናህ ጋር ጥራት ይገባህ ፡ ጌታችን ሆይ ማረኝ ፡፡ እዚህ ላይ ዱዓ ያብዛ ፡ ነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ስለሰሉ ( በሩኩእ ላይ ጌታችሁን አተልቁ ፡ በሱጁድ ላይ በዱዓ ተበራቱ ፡ እንደሚቀበላችሁ እርግጥ ነው ፡፡[2] ሰላቱ ግዴታም ይሁን ሱና ፡ ከአላህ የዚህችንም አለም የወዲያኛይቱንም አለም መልካም ሁሉ ይለምን ፡፡ ሱጁድ ሲወርድ ጡንቻዎቹን ከጎኑ ፤ ሆዱን ከታፋዎቹ ፤ ታፋዎቹን ከባቶቹ ያርቅ ፡ ክንዶቹን ከመሬት ከፍ ያድርግ ፡ ነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ስላሉ ( ሱጁድ ላይ ተስተካከሉ አንዳችሁ ክንዱን እንደ ውሻ መዘርጋት አይዘረጋ )[3]

[1] አልቡኻሪ አል አዛን (761) ፤ሙስሊም አሰላት (484) አቡ ዳውድ አሰላት (877) ፤ ኢብኑ ማጀህ ኢቃመቱ አሰላት ወ አሱነቱ ፊሃ (889) ፤ አህመድ (6/43) ፤ አነሰኢይ (1122)

[2] ሙስሊም አሰላት (479) አቡ ዳውድ አሰላት (876) ፤ አነሰኢይ አተጥቢቅ ( 1120) ፤ አዳረሚይ አሰላት (1325)፤ አህመድ (1/219)

[3] አልቡኻሪ አል አዛን (788) ፤ ሙስሊም አሰላት (493) ፤ አህመድ (3/192 )

10- አላሁ አክበር እያለ ጭንቅላቱን ቀና ያድርግ ፡ ግራ እግሩን አንጥፎ ይቀመጥበት ፡ ቀኝ እግሩን ያቁም ፡ እጆቹን በታፋውና ጉልበቱ ላይ ያኑር ፡ እንዲህም ይበል ፡( رَبِّ اغْفِرْ لِي وَارْحَمْنِي واهدني وَارْزُقْنِي وعافني وَاجْبُرْنِي ረቢግፊርሊ ወርሀምኒ ወህዲኒ ወርዙቅኒ ወዓፊኒ ወጅቡርኒ ፡[1] ጌታዬ ማረኝ ፤ እዘንልኝ ምራኝ ፤ ሲሳይ ስጠኝ ፤ ጤናኛ አድረርገኝ ፤ ጠግነኝ ፡፡) በዚህ መቀመጡ ላይ ይረጋጋ ፡፡

11- ሁለተኛውን ሱጁድ አላሁ አክበር እያለ ይውረድ ፡ በአንደኛው ሱጁድ እንዳደረገው ያድርግ ፡፡

12- አላሁ አክበር እያለ ጭንቅላቱን ከሱጁድ ያንሳ ፡ ቀለል ያለ መቀመጥን በሁለት ሱጁድ መሀል የተቀመጠውን ያህል ይቀመጥ ተወዳጅ ስለሆነ ፡ ይህም የእረፍት መቀመጥ ይባላል ፡ ቢተወው ችግር የለውም ፡ የራሱ የሆነ ዱዓእም ሆነ ዚክር የለውም ፡፡ ከዚያን ወደ ሁለተኛው ረካዓህ ብድግ ይበል ፡ ከተቻለው ጉልበቶቹን እየተደገፈ ካልቻለ መሬቱን እየተደገፈ ይቁም ፡ ከዚያ ፋቲሃን ከፋቲሃ በኋላ የገራለትን ሌላ የቁርዓን አንቀጾችን ይቅራ ፡፡ ከዚያን በአንደኛው ረከዐህ እንዳደረገው ያድርግ ፡፡

**13–** ሰላቱ ባለ ሁለት ረከዐህ ፡ እንደ ሱብሂ ፤ ጁምዐህ እና የዒድ ሰላቶች አይነት ከሆነ ፡ ሁለተኛውን ረከዐህ ጨርሶ ከሁለተኛው ሱጁድ ቀና እንዳለ ፡ ቀኝ እግሩን አቁሞ ግራ እግሩን አንጥፎ ይቀመጥ ፡ ቀኝ እጁን በቀኝ ታፋው አስቀምጦ ፡ አመልካች ጣት ስትቀር ሌሎችን ይጨብጣቸው ፡ በእሱዋ የተውሂድን (አላህ በብቸኝነት ተመላኪ መሆኑን ) ይጦቅምባታል ፡ ከቀኝ እጁ ትንሽዋንና የቀለበት ጣቱን ጨብጦ የመሀል ጣቱንና አውራ ጣቱን ክብ አድርጎዋቸው በአመልካች ጣቱ ቢጦቅምም ጥሩ ነው ፡፡ ሁለቱም አይነት ከነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ተዘግቦዋልና ፡ አንዴ ይህንን አንዴ ያንን ቢል ይመረጣል ፡፡ ግራ እጁን በግራ ታፋውና ጉልበቱ ላይ ያኑር ፡ ከዚያን በዚህ አቀማመጥ ሁኖ ተሸሁድን ይቅራ ፡እሱም ፡- (*አተሂያቱ ሊላሂ ወአሰለዋቱ ወጠይባቱ ፡ አሰላሙ አለይከ አዩሀ አነብዩ ፡ ወረህመቱላሂ ወበረካቱሀ ፡ አሰላሙ አለይና ወአላ ኢባዲላሂ አሳሊሂን ፡ አሽሀዱ አላ ኢላሀ ኢለ ላህ ፡ ወአሽሀዱ አነ ሙሀመደን አብዱሁ ወረሱሉሁ ፡-* ከዚያን የሚቀጥለውንም ይበል - *አላሁመ ሰሊ አለ ሙሀመድ ወአላ ኣሊ ሙሀመድ ከማ ሰለይተ አላ ኢብራሂመ ወአላ ኣሊ ኢብራሂመ ፡ ኢነከ ሀሚዱመጂድ ፡ ወባሪክ አላ ሙሀመዲን ወአላ ኣሊ ሙሀመዲን ከማ ባረክተ አላ ኢብረሂመ ወአላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢነከ ሀሚዱመጂድ*)፡፡

( اَلتَّحِيَّاتُ لِلَّهِ , وَالصَّلَوَاتُ , وَالطَّيِّبَاتُ , اَلسَّلَامُ عَلَيْكَ أَيُّهَا اَلنَّبِيُّ وَرَحْمَةَ اَللَّهِ وَبَرَكَاتُهُ , اَلسَّلَامُ عَلَيْنَا وَعَلَى عِبَادِ اَللَّهِ اَلصَّالِحِينَ , أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اَللَّهُ , وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ ، اللهم صلى على محمد وعلى آل محمد كما صليت على إبراهيم وآل إبراهيم إنك حميد مجيد وبارك على محمد وعلى آل محمد كما باركت على إبراهيم وآل إبراهيم إنك حميد مجيد )[2]

[1] አቡ ዳውድ አሰላት (850) ፤ ኢብኑ ማጀህ ኢቃመቱ አሰላት ወ አሱነቱ ፊሃ (898) ፤ አቱርሙዚይ አሰላት (284)

[2] አልቡኻሪ አል አዛን (797) ሙስሊም አሰላት ፤ (402) አቡ ዳውድ አሰላት (968) ፤ ኢብኑ ማጀህ ኢቃመቱ አሰላት ወ አሱነቱ ፊሃ (899) ፤ አቱርሙዚይ አኒካህ (1105) ፤ አነሰኢይ አሰህው ( 1298) ፤ አዳረሚይ አሰላት (1340)፤ አህመድ (1/428 )

ትርጉሙ ፡- ክብር ፤ ስግደትም ፤ መልካምነትም ፤ ለአላህ ይገባው ፡ አንተ ነብይ (የአላህ ) ሰላም ፤ በረከቱም ፤ እዝነቱም ፡ ባንተ ላይ ይሁን ፡፡ (የአላህ ) ሰላም በእኛ እና በደጋግ የአላህ ባርያዎች ላይ ይሁን ፡ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ ማንም የለም ብዬ እመሰክራለሁ ፡ ሙሀመድ የአላህ ባርያውና መልእክተኛው ነው ብዬ እመሰክራለሁ ፡ አላህ ሆይ በሙሀመድ ላይ ውዳሴህን አስፍን ፡ በሙሀመድ ቤተሰብም እንዲሁ ፡ በኢብራሂምና በቤተሰቡ ውዳሴህን እንዳሰፈንክ ፡አላህ ሆይ በሙሀመድ ላይ በረከትህን አስፍን ፡ በሙሀመድ ቤተሰብም እንዲሁ ፡ በኢብራሂምና በቤተሰቡ በረከትህን እንዳሰፈንክ ፡፡ ከአራት ነገሮች እንዲህ በማለት በአላህ ይጠበቅ እነሱም ፡- (*አላሁመ ኢኒ አኡዙ ቢከ ሚን አዛቢ ጀሀነም ወሚን አዛቢል ቀብር ወሚን ፊትነቲል መህያ ወል መማቲ ወሚን ፊትነቲ አል መሲሂ አደጃል ፡፡* اَللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ جَهَنَّمَ , وَمِنْ عَذَابِ اَلْقَبْرِ , وَمِنْ فِتْنَةِ اَلْمَحْيَا وَالْمَمَاتِ , وَمِنْ فِتْنَةِ اَلْمَسِيحِ اَلدَّجَّالِ )[1]

[1] አልቡኻሪ አል ጀናኢዝ (1311) ፤ ሙስሊም አል መሳጂድ ወመዋዲኡ አሰላት (588) አቡ ዳውድ አሰላት (983) ፤ ኢብኑ ማጀህ ኢቃመቱ አሰላት ወ አሱነቱ ፊሃ (909) ፤ አቱርሙዚይ አደአዋት (3604) ፤ አነሰኢይ አል ኢስተቲአዘህ ( 5513) ፤ አዳረሚይ አሰላት (1344)፤ አህመድ (2/454)

ጌታዬ ሆይ እኔ ፡ ከገሀነም ቅጣት ፤ ከቀብር ቅጣት ፤ ስኖርም ስሞትም ከሚገጥመኝ ፈተና ፤ ከመሲህ አደጃልም ፈተና ፡ባንተ እጠበቃለሁ፡፡ ከዚያ የፈለገውን ከዚች አለም እና ከወዲያኛይቱዋ አለም መልካም ዱዓ ያድርግ ፡፡ ለወላጆቹ ወይም ለሌላ ለሙስሊም ዱዓ ቢያደርግ ችግር የለውም ፡ -የሚሰግደው ሰላት ሱና ወይም ግዴታ ቢሆንም እኩል ነው ፡፡ ኢብኑ መስኡድን ስለ ተሸሁድ ከነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ይዘው ያስተማሩት ነገር ሁሉንም ያካታል ፡ እሱም ፡- (ከዚያን ደስ ያለውን ዱዓ መርጦ ያድርግ ፡፡ በሌላ አባባል ፡ከዚያን ከልመና የፈለገውን መረጦ ይጠይቅ ፡፡) ይህ አባባል በዚችም አለም በወዲያኛውም አለም ለባርያው የሚጠቅምን ነገር በሙሉ ያካትታል ፡፡ ከዚያን በስተቀኙ ከዚያም በስተግራው እንዲህ እያለ ያሰላምታል ፡ አሰላሙ አለይኩም ወረህመቱላሂ ፡ (አሰላሙ አለይኩም ወረህመቱላሂ السَّلامُ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَةُ اللهِ السَّلامُ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَةُ اللهِ )

14– ሰላቱ እንደ መግሪብ ባለሶስት ረከአህ ወይም እንደ ዙህር ፤ አሱር ፤ እና ኢሻእ ባለ አራት ረከአህ ከሆነ ፡ ከሁለተኛው ረከዐህ በኋላ ቅድም የተጠቀሰውን ተሸሁድ ያንብብ በነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ላይ ሰለዋት ከማድረግ ጋር ፡ ከዚያን አላሁ አክበር እያለ ሁለት እጆቹን ወደ ትከሻው ወይም ጆሮው እያቅጣጨ በጉልበቶቹ በመደገፍ ብድግ ብሎ ይቁም ፡ ከዚህ ቀደም እንዳለፈው ቀጥ ብሎ ከቆመ በኋላ ሁለት እጆቹን ደረቱ ላይ ያኑር ፡ ከዚያ ፋቲሃን ብቻ ይቅረ ፡ አንዳንዴ በዙህር ሰላት በሶስተኛውና አራተኛው ረከዐህ ላይ ከፋቲሃ በሆላ ሌላ የቁርዓን አንቀጾችን ቢቀራ ችግር የለውም ፡ ይህን የሚያመላክት ነገር ከሰሃባው አቢ ሰኢድ ረዲየላሁ አንሁ ተይዞ ከነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ስለተገኘ ፡፡ ከሁለተኛው ተሸሁድ በኋላ በነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ሰለዋት ማድረግ ቢተው ችግር የለውም ፡ ምክንያቱም እሱ በመጀመሪያው ተሸሁድ ተወዳጅ ነው እንጂ ግዴታ አይደለም ፡፡ በባለ ሁሉት ረከኣዎች አሰጋገድ ላይ እንዳለፈው ፡ ከመግሪብ ሶስተኛው ረከዐህ በኋላ እንዲሁም ከዙህር ፤ አሱር እና ኢሻእ ሰላት አራተኛው ረከአህ በኋላ ተሸሁድ ይቀመጣል ፡፡ ከዚያን ወደ ቀኙ እና ግራው በመዞር ያሰላምታል ፡፡ ከዚያን - አሰጋጅ - ኢማም ከሆነ ወደ ሰው ሳይዞር ፡የሚከተለውን ይላል ፡- *(አላሁመ አንተ አሰላም ወሚንከ አሰላም ፡ ተባረክተ ያ ዘልጃላሊ ወል ኢክራም* اَللَّهُمَّ أَنْتَ اَلسَّلَامُ وَمِنْكَ اَلسَّلَامُ . تَبَارَكْتَ يَا ذَا اَلْجَلَالِ وَالْإِكْرَامِ )[1]

---

[1] ሙስሊም አልመሳጂድ ወመዋዲኡ አሰላት (591) አቡ ዳውድ አሰላት (1512) ፤ ኢብኑ ማጀህ ኢቃመቱ አሰላት ወ አሱነቱ ፊሃ (928) ፤ አቱርሙዚይ አሰላት (300) ፤ አዳረሚይ አሰላት (1348)፤ አህመድ (5/280 )

15- ጌታዬ ሆይ አንተ ሰላም ነህ ሰላምም ካንተ ነው የልቅናና የልግስና ባለቤት የሆንክ እንዲሁም የተባረክ ነህ ፡፡ከዚያን እንዲህ ይበል ፡- *(ላ ኢላሀ ኢላ አላሁ ወህደሁ ላ ሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምዱ ወሁወ አላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር ፡ አላሁመ ላ ማኒአ ሊማ አእጠይተ ወለ ሙዕጢየ ሊማ መነዕተ ፡ ወላ የንፈኡ ዛ አልጀዲ ሚንከ አል ጀዱ ፡ላ ሀውለ ወላ ቁወተ ኢለ ቢላሂ ፡ ላ ኢላሀ ኢላ አላህ ፡ወላ ነእቡዱ ኢላ ኢያሁ ለሁ አኒእመቱ ወለሁ አል ፈድሉ ፡ ወለሁ አሰናኡ አል ሀሰኑ ፡ ላኢላሀ ኢላ አላሁ ሙኽሊሲና ለሁ አዲን ፡ ወለው ከሪሀ አል ካፊሩን ፡፡* لا إِلَهَ إِلا اللَّهُ وَحْدَهُ لا شَرِيكَ لَهُ ، لَهُ الْمُلْكُ ، وَلَهُ الْحَمْدُ ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ ، اللَّهُمَّ لا مَانِعَ لِمَا أَعْطَيْتَ ، وَلا مُعْطِ لِمَا مَنَعْتَ ، وَلا يَنْفَعُ ذَا الْجَدِّ مِنْكَ الْجَدُّ ، لا حولَ ولا قُوَّةَ إلا بِاللهِ ، لا إلهَ إلا اللهُ ، ولا نَعبُدُ إلا إيَّاه ، لَهُ النِّعْمَةُ ، ولَهُ الفَضْلُ ، ولَهُ الثَّنَاءُ الحَسَنُ ، لا إلهَ إلا الله مُخْلِصينَ له الدِّينَ ، وَلَو كَرِهَ الكافرون )[1]

[1] አልቡኻሪ አል አዛን (808) ፤ ሙስሊም አልመሳጂድ ወመዋዲኡ አሰላት (593) አቡ ዳውድ አሰላት (1505) ፤ አነሰኢይ አሰህው ( 1341)) ፤ አዳረሚይ አሰላት (1349)፤ አህመድ (4/250)

16- ከአላህ በስተቀ በእውነት የሚመለክ ማንም የለም ፡ እሱ ብጤ የለውም ንግስና እና ምስጋና ለሱ ብቻ ተገባ ፡ እሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው ፡ ጌታዬ ሆይ አንተ ለሰጠሀው ከልካይ የለውም ፡ አንተ ለከለከልከው ሰጭ የውም ፡ ባለ ልቅና ልቅናው አያብቃቃውም የሚያብቃቃው አንተን መታዘዝ ብቻ ነው ፡ ከአላህ በስተቀር ብልሃትም ሆነ ጉልበት ያለው ማንም የለም ፡ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ ማንም የለም ፡ እሱን በስተቀር አናመልክም ፡ ጸጋ ሁሉ የሱ ነው ፡ መቸርም የሱ ነው ፡ ምርጥ ውዳሴም ለሱ ይገባው ፡ ከሃዲዎች ቢጠሉም ከአላህ በስተቀ በእውነት የሚመለክ ማንም የለም ፡ ታኘነትን ሀይማኖትን ለሱ ብቻ በጥራት እናደርጋለን ፡፡ ከዚያን ሰላሳ ሶስት ግዜ ፡ ሱብሃነ አላሁ እንዲሁም አልሀምዱ ሊላህ እንዲሁም አላሁ አክበር ይበል ፡ መቶ ለመሙላት እንዲህ ይበል ፡- ((*ላ ኢላህ ኢላ ላሁ ወህደሁ ላ ሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምዱ ወሁወ አላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር* ፡ لا إِلَهَ إِلا اللَّهُ وَحْدَهُ لا شَرِيكَ لَهُ ، لَهُ الْمُلْكُ ، وَلَهُ الْحَمْدُ ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ

ከአላህ በስተቀ በእውነት የሚመለክ ማንም የለም ፡ እሱ ብጤ የለውም ንግስና እና ምስጋና ለሱ ብቻ ተገባ ፡ እሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው ፡፡ ከዚያን አል ኩርሲይ አንቀጽን ፡ ቁል ሁ አላሁ አሀድ ... ፡ ቁል አኡዙ ቢረቢ አፈለቅ... ፡ ቁል አኡዙ ቢረቢ አናስ... ይቅራ ፡ ይህን ሁሌም ከሰላት በሆላ ይተግብር ፡ እነዚህን ሶስቱን ምእራፎች ፡ ከመግሪብ እና ሱብሂ ሰላት በኗላ ሶስት ግዜ መደጋገሙ ይወደዳል ፡ ይህን የሚያመላክት ዘገባ ከነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ተዘግቦዋልና ፡፡ እነዚህ አዝካሮች (ውዳሴዎች) በፍላጎት የሚደረጉ ናቸው ግዴታ አይደሉም ፡፡

ሙስሊም ለሆነ ወንድና ሴት ከዙህር በፊት አራት ረክአህ ከበስተሆላው ሁለት ረክአህ ፤ ከመግሪብ ሰላት በኗላ ሁለት ረክአህ ፤ ከኢሻእ ሰላት በኗላ ሁለት ረክአህ እና ከሱብሂ ሰላት በፊት ሁለት ረክአህ መስገድ የተደነገገ ነው ፡፡ ጠቅላላው አስራ ሁለት ረክአህ ነው ፡፡ እነዚህ ሰላቶች ረዋቲብ ቆሚ ተከታዮች - ይባላሉ ፡፡ ምክንያቱም ፡ነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም አገር እስካሉ ድረስ ያዘወትሩዋቸው ነበር ፡፡ ጉዞ ላይ ሲሆኑ ከሱብሂ ሱና እና ከዊትር በስተቀር አይሰግዱም ነበር ፡ እኚህን በሰፈርም በመንገድም ያዘወትሩዋቸው ነበር ፡፡ እነዚህ ራቲባህ ሰላቶች እና ዊትር ሰላትን በቤት መሰገዳቸው ይመረጣል መስጅድ ቢሰገዱም ችግር የለውም ፡፡ ነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል ፡- ( የአንድ ሰው በላጭ ሰላቱ ቤት ሚሰግደው ነው ግዴታ ሰላቶች ሲቀሩ ) [1]

[1] አልቡኻሪ አል አደብ (5762) ፤ ሙስሊም ሰላት አል ሙሳፊሪና ወቀስሩሃ (781) አቡ ዳውድ አሰላት (1447) ፤ አቱርሙዚይ አሰላት (361) ፤ አነሰኢይ ቂያሙ አልሊ ወተጠውኡ አነሃር ( 1599) ፤ ማሊክ አኒዳእ ሊ አሰላት (293) ፤ አዳረሚይ አሰላት (1366)፤ አህመድ (5/186)

ለእነዚህ ረከኣዎች ትኩረት ማድረግ እና መጠባበቅ ጀነት ከሚያስገቡ ምክንያቶች ውስጥ ነው ፡ ነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋልና ፡- ( በቀኑና በማታው አስራ ሁለት ረከአህ ሰላት በፍላጎቱ የሰገደ አላህ በጀነት ቤት ይገነባለታል )። [1]

[1] ሙስሊም ሰላት አል ሙሳፊሪና ወቀስሩሃ (1199/1198) አቡ ዳውድ አሰላት (1059) ፤ አነሰኢይ ቂያሙ አልሊ ወተጠውኡ አነሃር ( 1773) ፤ አህመድ (6/327)

ሙስሊም በትክክለኛ ዘገባቸው ዘግበውታል ፡፡ ከአስር ሰላት በፊት አራት ክአህ ፤ ከመግሪብ ሰላት በፊት ሁለት ረክአህ ፤ ከኢሻእ ሰላት በፊት ሁለት ረክአህ ፡ ቢሰገድ ፡ ጥሩ ነው ፡ ምክንያቱም ይህን የሚያመላክት ነገር ከነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ተዘግቦዋል ፡ ከዙህር በፊት አራት ከበስተኖላም አራት ረክአህ ቢሰግድ ጥሩ ነው ፡ ነብዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ስላሉ ፡- ( ከዙህር በፊት አራት ረክአህ ከዙህር በኖላ አራት ረክአህ በመስገድ ላይ ቱክረት ያደረገ አላህ እሱን በእሳት ላይ እርም ያደርገዋል ፡፡)[23] ከኡሙ ሀቢባህ ረዲየላሁ አንሃ ይዘው ፡ ኢማሙ አህመድ እና የሱነን ባልተቤቶች -ዘጋቢዎች- በትክክለኛ ዘገባቸው ዘግበውታል ፡፡ የዚህ ሀዲስ መልእክት ፡ ከመደበኛው ከበስተኖላ ሱና ላይ ሁለት ረክአህ ይጨምራል ማለት ነው ፡ ምክንያቱም መጀመሪያውኑ የዙህር መደበኛው ሱና አራት ረክአህ ከበስተፊት ሁለት ረክአህ ከበስተኖላ ነበር ፡ ከበስተኖላ ሁለት ረክአህ ሲጨምር በኡሙ ሀቢባ የተነገረውን ሀዲስ ቱሩፋት ያገኛል ማለት ነው ፡፡

የመግጠም ባለቤት አላህ ነው ፡፡

አላህ በነብያችን የአብደላህ ልጅ ሙሀመድ ውዳሴውንና ሰላሙን ያስፍንባቸው ፡ እንዲሁም በቤተሰቦቻቸው ፤ በባልደረቦቻቸው ፤ በመልካም በተከተላቸው ሁሉ እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ ይስፈንባቸው ፡፡

የጥናታዊ እውቀት ፤ የፈትዋ ፤ የምክር እና የጥሪ ቢሮዎች የበላይ ሀላፊ
አብዱ አል አዚዝ ብን አብዲላህ ብኑ ባዝ

[23]አቡ ዳውድ አሰላት (1077) ፤ አቱርሙዚይ አሰላት (393) ፤ አህመድ ባቂ ሙስነድ አል አንሳር (25547)